DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

# የትምህርት ዓመት 2020-21 የምዝገባ መመሪያ እና ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

በክልላችን የCOVID-19 ስርጭት እንዲሻሻል ለመርዳት፣ ሁሉም የDCPS ትምህርት ቤት ህንፃዎች በአሁኑ ወቅት ዝግ የሆኑና የርቀት ትምህርትም በቤት ውስጥ አሁን ለሚማሩ ተማሪዎች እየተሰጠ ይገኛል። ስለ ምዝገባ ሂደቶች እና የማብቂያ የጊዜ ገደብን በተመለከተ የተሰጠውን ይፋዊ አዲስና ማሻሻያዎችን፣ እባክዎን ከዚህ በታች ያግኙ። እነዚህ መመሪያዎች በስራ ላይ የሚውሉት፣ የትምህርት ቤት ህንፃዎች እንደገና እስከሚከፈቱበት ቀን እስከ ሰኞ፣ ሚያዝያ 19 (April 27) ድረስ ይሆናል።

በተቻለ ፍጥነት ምዝገባን ጀምረን፣ ቤተሰቦቻችንን ተመራጭ በሆነ መንገድ ለማገልገል እና አዳዲስ ተማሪዎችን ወደ ማህበረሰባችን ለመቀበል፣ DCPS ይተጋል! ከ51,000 በላይ ተማሪዎችን ለማገልገል በመቻላችን ኩራት ይሰማናል፤ እንዲሁም የትምህርት ዓመት 2020-2021 (SY20-21) ከቤተሰብዎ ጋር በመሆን ለመጀመር በጉጉት እንጠብቃለን።

ለSY20-21 ምዝገባ በኤሌክትሮኒክ ማስገባት የሚቻልበትን ሂደቶች ለመክፈት ጠንክረን እየሰራን የምንገኝ እና ዓላማችንም፣ በተቻለ መጠን ሚያዝያ 19 (April 27) ሳያልፍ፣ ይህንን አማራጭ ለቤተሰቦች ማቅረብ ነው። ስለሚኖሩ አዲስና ማሻሻያዎች፣ ተጨማሪ መረጃን እንዳገኘን ማሳወቃችንን እንቀጥላለን።

ሐሙስ፣ መጋቢት 17 ቀን 2012 ዓ.ም (March 26, 2020) በተገለጸው መሠረት፣ የሚከተሉት ወቅታዊ መረጃዎች ናቸው።

በSY20-21 የምዝገባ ሂደት እና የማብቂያ የቀን ገደቦችን በተመለከተ የተደረጉ ለውጦችን ጠቅለል ብለው ቀርበዋል:

- የሎተሪ ውጤቶች፣ አርብ መጋቢት 18 (March 27) ቀን በይፋ ለሕዝብ ይገለፃል።
- በግንባር ቀርቦ መመዝገብ የሚጀምረው፣ የትምህርት ቤት ህንፃዎች ሲከፈቱ፣ ሰኞ ሚያዝያ 19 (April 27) ይሆናል።
- ወላጆች እስከ እሮብ፣ ግንቦት 19 (May 27) ቀን ድረስ፤ (የDCPS ትምህርት ቤት ህንፃዎችን ለመክፈት የጊዜ ሰሌዳ ከተያዘበት፣ ከአንድ ወር በኋላ) ለመመዝገብ እና ቦታቸውን ለመያዝ መጠየቅ ይቻላሉ።
- የOSSE ደንቦችን በተከተለ መልኩ፣ ለSY20-21 ምዝገባ በኤሌክትሮኒክ ለማስገባት የሚቻልበት አማራጮች ላይ፣ DCPS እየሰራ ይገኛል። ዓላማው፣ ሚያዝያ 19 (April 27) ሳይደርስ፣ ይህንን አማራጭ ለቤተሰቦች ማቅረብ ነው።
- DCPS፣ የSY20-21 የምዝገባ ጥራዝ (Packet) በኦንላይን የሚለጥፍና የትምህርት ቤት ህንፃዎች ሰኞ፣ ሚያዝያ 19 (April 27) እንደገና ሲከፈቱ፣ ከትምህርት ቤቶች ጋር ያጋራል። የኤሌክትሮኒክ ምዝገባ ማስገቢያ ምርጫው ከተጠቀሰው ቀን በፊት ከጀመረ፣ DCPS የSY20-21 የምዝገባ ጥራዝ (Packet) በኦንላይን ወዲያውኑ ይለጥፋል።

## ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች (FAQs)

1. **በ'My School DC' ሎተሪ ውጤቶች የጊዜ ሰሌዳ ላይ፣ ይህ መዘጋት ምን ተፅዕኖ ይኖረዋል?**
   ለSY20-21፣ ለመመዝገብ እና በሎተሪ የተዛመዱበትን ቦታ ለማግኘት እስከ **እሮብ ግንቦት 19 (May 27)** ተራዝሟል። ይህም፣ ትምህርት ቤቶችን እንደገና ለመክፈት ከታቀደበት የጊዜ ሰሌዳ፣ አንድ ወር በኋላ ማለት ነው።

2. **ተማሪዬን ለSY20-21፣ መቼ እና እንዴት ማስመዝገብ እችላለሁ?**
   DCPS ምዝገባን በተቻለ ፍጥነት ለመክፈት ቁርጠኝነቱን ያሳያል! በግንባር ቀርቦ መመዝገብ፣ የትምህርት ቤት ህንፃዎች እንደገና ሲከፈቱ፣ ሰኞ ሚያዝያ 19 (April 27) ቀን ይጀምራል። ለSY20-21 ምዝገባ በኤሌክትሮኒክ ለማስገባት የሚቻልበትን ሂደቶች ለመክፈት ጠንክረን እየሰራን የምንገኝ እና ዓላማችንም፣ ሚያዝያ 19 (April 27) ሳያልፍ፣ ይህንን አማራጭ ለቤተሰቦች ማቅረብ ነው። የሚኖሩትን አዲስና ማሻሻያዎችን ማሳወቃችንን እንቀጥላለን!

3. **ትምህርት ቤቶች እስከ ሚያዝያ 19 (April 27) በመዘጋታቸው ምክንያት፣ ተማሪዎች ያገኙትን የተዛመደ ቦታቸውን እንዲያጡ ያደርጋቸዋል?**
   ሁሉም የተዛመዱ ቦታዎች እስከ እሮብ፣ ግንቦት 19 (May 27) ድርስ ዋስትና አላቸው። ቤተሰቦች እስከ ግንቦት 19 (May 27) መመዝገብ እና ቦታቸውን መጠየቅ አለባቸው። ለማስታወስ ያህል፣ ሁሉም ቤተሰቦች፣ ከK እስከ 12ተኛ ክፍል በክልል-ወሰን ትምህርት ቤት ውስጥ (in-boundary school) ውስጥ ቦታ ለማግኘት ምንጊዜም ቢሆን ዋስትና አላቸው።

**4. ተማሪዬ ከተጠባባቂ ዝርዝር (waitlist) ውስጥ ከእሮብ ግንቦት 19 (May 27) በፊት ቢጠሩ፣ ለመመዝገብ እና የተሰጠውን ቦታ ለመቀበል ምን ያህል ጊዜ ይኖራቸዋል?**
ማንኛውም ከተጠባባቂ ዝርዝሩ (waitlist) ውስጥ ከግንቦት 19 (May 27) ከአምስት ቀናት በላይ በቅድሚያ፣ ቦታውን እንዲወስዱ የተጠየቁ ተማሪዎች፣ ለመመዝገብ እና የተሰጠውን ቦታ ለመቀበል የሚሰጣቸው ግዜ እስከ እሮብ ግንቦት 19 (May 27) ይሆናል።

**5. የDCPS የSY20-21 የምዝገባ ጥራዝ (Packet) እና ሌሎች ከምዝገባ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ቅጾች የት ማግኘት እችላለሁ?**
DCPS፣ የSY20-21 የምዝገባ ጥራዝ (Packet) በኦንላይን የሚለጥፍና የትምህርት ቤት ህንፃዎች ሰኞ፣ ሚያዝያ 19 (April 27) እንደገና ሲከፈቱ፣ ከትምህርት ቤቶች ጋር ያጋራል። የኤሌክትሮኒክ ምዝገባ ማስገቢያ ምርጫው ከተጠቀሰው ቀን በፊት ከጀመረ፣ DCPS የSY20-21 የምዝገባ ጥራዝ (Packet)፣ በDCPS የምዝገባ ድህረ-ገጹ ላይ የኤሌክትሮኒክ ምዝገባ ማስገቢያ ምርጫው ሲጀመር ይለጥፋል።

**6. የዲሲ ነዋሪነታቸውን ቤተሰቦች እንዴት ማረጋገጥ እንዳለባቸው በተመለከተ፣ የተደረጉ ለውጦች አሉ?**
ለቤተሰቦች፣ በSY20-21 በሚቀርቡ መስፈርቶች ላይ ምንም የተደረገ ለውጥ የለም፣ ነገር ግን አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን ለማስገባት አማራጭ ዘዴዎች ይቀርባሉ። አሁንም ቢሆን፣ ሁሉም ቤተሰቦች የDCPS የምዝገባ ጥራዝ (packet) መሙላት፣ የዲሲ ነዋሪነታቸውን ማረጋገጥ፣ እና ሁሉንም ሰነዶች ወደ ትምህርት ቤታቸው ማስገባት አለባቸው።

የትምህርት ቤት ህንፃዎች እስከ አርብ ሚያዝያ 16 (April 24) ቀን ድረስ በመዘጋታቸው ምክንያት፣ ቤተሰቦች የምዝገባ ወረቀቶችን ወደየትምህርት ቤቶቻቸው፤ ሰኞ፣ ሚያዝያ 19 (April 27) ከመሆኑ በፊት በግንባር ቀርበው ማስገባት አይችሉም። ቤተሰቦችንና ትምህርት ቤቶችን ለመርዳት፣ ሁሉንም የምዝገባ ሰነዶችን፣ የዲሲ ነዋሪነት ወረቀቶችን ጨምሮ ለማስገባት እና ቤተሰቦች የኤሌክትሮኒክ ፊርማ (e-signature) የማስገባት አማራጮች እንዲኖሯቸው፣ DCPS ተገቢ የሆነ ሂደት ያለው የኦንላይን ማስገቢያ ለማስገኘት እየሰራ ይገኛል። ዓላማው፣ ሰኞ ሚያዝያ 19 (April 27) ሳይደርስ፣ ይህንን አማራጭ ለቤተሰቦች እና ለትምህርት ቤቶች ማቅረብ ነው።

**7. ለSY20-21፣ ከጤና ጋር ግንኙነት ያላቸው ምዝገባዎችን ለማድረግ የሚፈለጉ መስፈርቶች ላይ የተደረጉ ለውጦች አሉ?**
ከዚህ በላይ የተገለጸው የምዝገባ ሂደት ለውጦች እንዳሉ ሆኖ፣ አሁኑ ወቅት OSSE፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች፣ የአለም ዓቀፍ የጤና ሰርተፊኬት (Universal Health Certificates) እና የአፍ ጤና እገዛዎች (Oral Health Assessments) መረጃዎችን በምዝገባ ወቅት ሳይሆን፣ በSY20-21 መጀመሪያ ላይ እንዲያቀርቡ ይጠይቃል። ለማስታወስ ያህል፣ ሁሉም ተማሪዎች ትምህርት ቤት ውስጥ ገብቶ ለመማር፣ የክትባት (immunizations) ማረጋገጫዎቻቸው ወቅታዊነቱን የጠበቁ መሆን አለበት።

**8. የ2020 የምዝገባ እለተ ቅዳሜ፣ አሁንም ይካሄዳል?**
የለም። ከዚህ ቀደም ቅዳሜ ሚያዝያ 17 (April 25) ቀን፣ ሊካሄድ ታቅዶ የነበረው – የ2020 የምዝገባ እለተ ቅዳሜ፤ ተሰርዟል።

**9. ስለምዝገባው ተጨማሪ ጥያቄዎች ካሉኝ፣ ማንን ነው የማነጋግረው?**
ጥያቄዎች ካለዎት፣ የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች እንዲከተሉ እናበረታታለን:

- የDCPS የምዝገባ ድህረ-ገጽን ይጎብኙ።
- የምዝገባ ቡድኑን በenroll@k12.dc.gov ወይም በ(202) 478-5738 ያነጋግሩ።
- ከሎተሪ ጋር የተገናኙ ጥያቄዎችን ብቻ ለመጠየቅ፣ የ'My School DC'ን በ(202) 888-6336 ወይም በinfo.myschooldc@dc.gov ያነጋግሩ።